በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1993 በጀት ዓመት

# የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ

አዲስ አበባ

ሚያዝያ 1992

በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# *የ1993 በጀት ዓመት*

# *የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ*

አዲስ አበባ

ሚያዝያ 1992

# ማውጫ


| አርዕስት | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | መግቢያ | 1 |
| 2. | የ1992 የስምንት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ | 2 |
| 3. | የ1993 የሚካሄድ ጥናት የዕቅድ ዓላማዎች የአፈጻጸም ስልቶች | 5 |
| 4. | የ1993 ዕቅድ ይዘት | 7 |
| 5. | የ1993 ካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ | 8 |
| 6. | የ1993 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት | 12 |
| 7. | የ1993 ጥናቶች ግብና መግለጫ | 21 |
| 8. | የ1993 የሰው ኃይል ፍላጎት | 31 |
| 9. | የ1993 ጥናቶች መርሀ-ግብር | 31 |
| 10. | የ1993 የካፒታል በጀት መጠየቂያ ቅጽ | 39 |
| 11. | ትኩረትና መመሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች | 47 |

# 1993 የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ

## 1. መግቢያ

የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና ከፍ ለማድረግ የሚረዱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን ለመቀየስ፣ መንግሥት ለሚወጥናቸው ዕቅዶችና ለሚያዘጋጃቸው ፕሮግራሞች እነዚህም ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በተግባር ላይ ሲውሉ ለመከታተልና ለመገምገም በየዘርፉ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ሊገልጽ የሚችል ወቅታዊ፣ የተሟላና አስተማማኝ የሆነ ስታቲስቲካዊ መረጃ መኖር ወሳኝ ነው። እንደዚሁም የእነዚህ መረጃዎች መኖር በተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ መስኮች ጥናቶችና መርምሮች ለማካሄድ ይረዳሉ።

ስለሆነም የአገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎትና በማሟላት ረገድ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት ስለሆነ ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ መረጃ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠርና በየጊዜው የተሻሻለ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ የመረጃ ፍላጎትን ከፍተት ለማጥበብ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። በመሆኑም የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለዚህ ዓላማ ስኬታማ መሆን ብሎም ለስታቲስቲክስ መረጃ ክምችት መዳበር ባደረገው ያላሰለሰ ጥረት በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲሞግራፊ - ነክ መረጃዎች በመሰብሰብ፣ በማቀነባበርና በመተንተን ሪፓርቶቹን አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች አሠራጭቷል። ከዚህም አኳያ የመንግሥትን የትኩረት አቅጣጫና የመረጃ ፍላጎትን በማጤኝ እንደዚሁም የመሥሪያ ቤቱን አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት በ1993 በጀት ዓመት ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ቢጠኑ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ፍላጎት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው የታመነባቸውን ጥናቶች ለማካሄድ የ1993 - 95 የስታቲስቲክስ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የ1993 ዕቅድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1993 በጀት ዓመት ለማካሄድ ያቀዳቸው ጥናቶች መሠረታዊ የሆኑ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ሕዝብ-ነክ መረጃዎችን የሚያስገኙ በመሆናቸው ውጤታቸው ለአገር አቀፍና ለብሔራዊ ክልሎች የስታቲስቲክስ መረጃ መዳበር፣ ሌሎች መ/ቤቶችና ድርጅቶች ወደፊት ለሚያዘጋጁዋቸው ዕቅዶችና ለሚያካሄዷቸው ምርምሮች ጥናቶቹ መነሻ በመሆን እንደሚያገለግሉ መ/ቤቱ ያምናል።

ይህ የአንድ ዓመት ዕቅድ የተዘጋጀው ከላይ የተጠቀሱት አጠቃላይ ዓላማዎች መሠረት በማድረግ ሲሆን ጥራዙም 11 ክፍሎች እንዲይዝ ተደርጓል። እነዚህም፡-

ክፍል 1 መግቢያ ሲሆን ክፍል 2 የመ/ቤቱን የ1992 በጀት ዓመት የስምንት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ይዟል። ክፍል 3 የ1993 የዕቅድ ዓላማዎችና የአፈጻጸም ስልቶችን የሚያሳይ ሲሆን፣ ክፍል 4 የ1993ን ዕቅድ ይዘት አካቷል። በክፍል 5 ደግሞ ለታቀዱት ጥናቶች ማስፈጸሚያ የሚውል የካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ ቀርቧል። እንደዚሁም ከክፍል 6 እስከ 10 ባሉት ውስጥ የ1993 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት፣ የ1993 የዕቅድ ግብ፣ የሰው ኃይል ፍላጎት፣ መርሐግብርና የካፒታል በጀት መጠየቂያ ቅጽ በቅደም ተከተል ተቀምጧል። በመጨረሻም በተጠቀሰው የበጀት ዓመት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ትኩረት ከሚሹ አበይት ጉዳዮች ውስጥ ዋናዋናዎቹ በክፍል 11 እንዲታዩ ተደርጓል።

## 2. የ1992 የስምንት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ

### 2.1 ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራምን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1992 በጀት ዓመት አሥራ አንድ አዳዲስ ጥናቶች ለማካሄድና በ1991 በጀት መረጃ ዓመት ተሰብስቦላቸው የመረጃ ቅንብርና የሪፓርት ዝግጅት ተግባራቸው ወደዚህ በጀት ዓመት የተሸጋገሩ ነባር ጥናቶች ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነበር። በዚህም መሠረት እስከ የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም ባሉት ስምንት ወራት ከአዲሶቹ ጥናቶች መሐል የ1992 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ተጠናቆ መረጃው በኮምፒዩተር ተቀንባብሮ ሪፓርቱም ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። እንደዚሁም የ1992 የግብርና ናሙና የመኸር ወቅት ጥናት መረጃ የመሰብሰቡ ተግባር ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን የመረጃ ቅንብሩ ተግባር በመጀመሩ እስካሁን የኤዲቲንግ ኮዲንግ ሥራ ተጠናቋል። እንደዚሁም የ1991 የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የዚሁ ዓመት የኮንስትራክሽንና የማዕድን ቁፋሮ ( Quarrying) ጥናቶች የመረጃ ቅንብራቸውና የሪፓርት ዝግጅታቸው ተግባር ተጠናቆ ውጤቶቹ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል። በተጨማሪም የአምራችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገጠርና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ እንደዚሁም የየወሩ የዋጋዎች ኢንዴክስ ዝግጅት ተግባር በወጣላቸው ፕሮግራም መሠረት እየተጠናቀቁ ናቸው። ከነባር ጥናቶች መሐል የ1991 የሰው ኃይል ጥናት የመረጃው የቅንብር ተግባር እንዲሁም የሪፓርት ዝግጅቱ ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛል። የዚሁ ዓመት በተጨማሪም የ1992 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት የመጀመሪያውና የሁለተኛው ዙር እና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የመረጃ ቅንብራቸው ሥራ እየተካሄደ ነው።

## 2.2 የዲሞግራፊና ጤና ጥናትን ( DHS) በተመለከተ

በአገሪቱ በናሙና በተመረጡ 540 የቆጠራ ቦታዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደው የዲሞግራፊና ጤና ጥናት ውጤት ተጠቃሚ ከሚሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ መ/ቤቶችና ድርጅቶች እንደዚሁም ከጥናትና ምርምር ተቋማትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተውጣጡ ባለሙያዎች አስተያየት ታክሎበትና ለጥናቱ አገልግሎት እንዲውል የተዘጋጀው የመጠይቅ ዝግጅት ተግባር ከማለቁም በተጨማሪ ለዚህ ሥራ በመስክ ለሚሳተፉ ሠራተኞች የሚሰጠው ሥልጠናም ተጠናቋል:: በመሆኑም የመስክ ሠራተኞቹ ባሁኑ ወቅት በአጥጋቢ ሁኔታ መረጃዎቹ በመሰብሰብ ላይ ናቸው::

## 2.3 የሰው ኃይል ቅጥርና ሥልጠናን በተመለከተ

በ1992 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,328 ቋሚና 2,329 የኮንትራት በጠቅላላ 3,657 ሠራተኞች ነበሩ:: በበጀት ዓመቱ ለመቅጠር ከታሰበው ተጨማሪ የሰው ኃይል እስከ የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ 112 ቋሚና 853 የኮንትራት በድምሩ 965 ሠራተኞች ተቀጥረዋል:: ከዚህም ሌላ አንድ ሠራተኛ ከሌላ ቦታ ወደ ባለሥልጣኑ መ/ቤት ተዛውረው የመጡ ሲሆን ከቋሚ ሠራተኞች መሐል 16 እንደዚሁም ከኮንትራት ሠራተኞች መካከል 873 በድምሩ 889 ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት ከነበረው የሰው ኃይል የተቀነሱ በመሆናቸው በበጀት ዓመቱ ስምንተኛ ወር መጨረሻ ላይ የነበረው የሰው ኃይል 1,425 ቋሚና 3,182 የኮንትራት በድምሩ 4,607 ሠራተኞች ናቸው::

መ/ቤቱ ዕቅዱን የማስፈጸም አቅም ካሉት ሠራተኞች የሥራ ብቃት ጋር በቀጥታ የተቆራኘ በመሆኑ የተለያየ ሥልጠና እንዲያገኙ አድርጓል:: በማድረግም ላይ ሲሆን ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. በሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፡- በግብርና ናሙና ጥናት፣ በዲሞግራፊና ጤና ጥናት በትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ በኮንስትራክሽንና ቁፋሮ ጥናት፣ በቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ እንደዚሁም በኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት ላይ ለሚሳተፉ በዋናው መ/ቤት የአሠልጣኞች ሥልጠና፣ በየቅ/ጽ/ቤቶች ደግሞ ለመረጃ ጥራት ተቆጣጣሪዎችና ለመረጃ ሰብሳቢዎች ስለ እያንዳንዱ ጥናት አጠቃላይ ግንዛቤ ያስጨበጠና ለመረጃ አሰባሰብ ሥራ ችሎታ የሚያዳብር ሥልጠና ተሰጥቷል::

ለ. በመ/ቤቱ ለሚገኙ የዳታ ኢዲተሮች፣ ኢንኮደሮችና መረጃ የማመሳከር ተግባር ለሚያከናውኑ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

ሐ. በአገር ውስጥ በሚሰጥ ሥልጠና ማለትም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሦስት ሠራተኞች ሁለት በስታቲስቲክስ አንድ በዲሞግራፊ በማስተርስ ዲግሪ ሥልጠና አጠናቀዋል። እንደዚሁም በውጭ አገር ማለትም ከጋና ሦስት፣ ከኡጋንዳ አራት ሠራተኞች በማስተርስ ዲግሪ ሥልጠናቸውን አጠናቀው ሲመለሱ አንድ ሠራተኛ ደግሞ ከታንዛኒያ በቅድመ ምረቃ ሠልጥኖ ዲፕሎም በመቀበል ተመልሷል። በሌላ በኩል በ1991 ከገቡት ሦስት ሠራተኞች በተጨማሪ በ1992 ዓ.ም ሌሎች ሦስት ሠራተኞች የማስተርስ ዲግሪ ለመከታተል አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የገቡ ሲሆን አምስት ሠራተኞች በቦትስዋና፣ እንደዚሁም አንድ ሠራተኛ ደግሞ በደቡብ አፍሪካ የማስተርስ ዲግሪ ትምህርት በመከታተል ላይ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ስድስት ሠራተኞች በስታቲስቲክስ ትምህርት የሠርተፊኬት ፕሮግራም በታንዛንያ በመከታተል ላይ ናቸው። እንደዚሁም አንድ ሠራተኛ በኢንፎርሜሽን ሳይንስ በድህረ ምረቃ የዲፕሎማ ፕሮግራም በመከታተል ላይ ናቸው።

## 2.4 <u>የፋይናንስ አጠቃቀምን በተመለከተ</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1992 በጀት ዓመት የተፈቀደለት ካፒታል በጀት ብር 34,023,200.00 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ብር 20,032,000.00 ሲሆን ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ብር 13,991,200.00 የተፈቀደ ነው።

ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ከተፈቀደው ውስጥ እስከ የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ ብረ 16,777,400.00 ወጪ ተደርጓል። አፈጻጸሙም ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 83.75% ነው። በልዩነት የሚታየው ብር 3,254,600.00 ለቀሪ ሥራዎች ማጠናቀቂያ የሚውል ይሆናል።

ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ከተፈቀደው ብር 13,991,200.00 ውስጥ እስከ የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ ብር 11,225,060.00 ወጪ ተደርጓል። ከቆጠራው የሙከራ ጥናት የዝግጅት ሥራዎች ማለትም የመስክ መገልገያ ዕቃዎች (ኮምፓስ ሜትር) እንደዚሁም መኪናዎች በ1991 በጀት ዓመት እንዲገዙ በዕቅድ

ተይዞ የነበረ ቢሆንም ዕቃዎቹ ከውጭ የሚመጡ በመሆናቸው የበጀት ዓመቱ ካለቀ በኋላ በ1992 በጀት ዓመት በመቅረባቸው በዚሁ ዓመት የተለያዩ ዕቃዎችን ባጠቃላይ ግብረና ቆጠራ ማስፈጸሚያ መግና በተመደበ በጀት በሚተካ እንዲሸፈን ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ወጪ የሆነው 80.23% ነው፡፡

## 2.5 በ1992 ዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ላይ ያጋጠሙ ችግሮች

የባለሥልጣኑ መ/ቤት የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ባደረገው ያላሰለሰ ጥረት እንደዚሁም ከመንግሥትና ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በሚደረግለት ድጋፍ ሲያጋጥሙ የነበሩ በርካታ ችግሮች እየተቃለሉለት ቢሆንም በተለይ አዲስ በተፈቀደው የመ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት ቁጥራቸው በዛ ያለ የኮንትራት ሠራተኞች በቋሚነት እንዲቀጠሩ በመወሰኑ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ይህ በዋናው መ/ቤትና በሃያ ሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኘው ሠራተኛ ጉዳይ ተከታትሎ የአስተዳደርና የፐርሶኔል ሥራ የሚያስፈጽም ሠራተኛ በበቂ ሁኔታ በዋናው መ/ቤትና በ22ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች መመደብ ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል ለረዥም ጊዜ ልምድ ያካበቱ የመ/ቤቱ ነባር ባለሙያዎች የተሻለ ክፍያ ለመፈለግ በፈቃዳቸው መ/ቤቱን ለቀው ስለሚሄዱ በመ/ቤቱ ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎች ቁጥር እየቀነሰ ከመሄዱም ሌላ ከገበያ የዚህ ዓይነት ሠራተኞችን ፈልጎ በመቅጠር ለመተካት አልተቻለም፡፡ እነዚህ በየጊዜው የሚለቁ ሠራተኞችን ለማቆየትም ሆነ ልምድ ያላቸውን ሠራተኞች ለመቅጠር የሚያስችል የተሻለ የደመወዝ እስኬል ለመ/ቤቱ እንዲፈቀድ ያስፈልጋል፡፡

# 3. የ1993 የሚካሄዱ ጥናቶች ዕቅድ ዓላማዎችና የአፈጻጸም ስልቶች

## 3.1 በ1993 የሚካሄዱ ጥናቶች ዓላማዎች

በ1993 የሚካሄዱ ጥናቶች ዕቅድና ዓላማዎች ከመ/ቤቱ አበይት ተግባራት ጋር የተቀናጁ ሆነው የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡፡

የአገሪቱን የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ዕቅድ ዝግጅቶች ክትትልና ግምገማ እንደዚሁም ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ የሚያገለግሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ በማቀነባበርና መረጃዎችን ተንተኖ ሪፓርት በማዘጋጀት ለመረጃ ተጠቃሚዎች ማሰራጨትን አጠቃላይ ዓላማው ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ፡-

- ለፕላን ዝግጅት፣ ለክትትልና ግምገማ፣ ለምርምር፣ ለፖሊሲ ቅየሳና ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሊያገለግሉ የሚችሉ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲሞግራፊ መረጃዎችን በተቀናጀ አሠራር ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

- በስታቲስቲክስ ሥራ አኳያ በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝና የሪፖርት ሥርዓት እንዲዘረጋ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣

- ወደፊት የሚኖረውን ሰፊ የስታቲስቲክስ የመረጃ ፍላጎት ከማሟላት አኳያ አመቺና ተስማሚ የሆኑ የስታቲስቲክስ ሥራዎች ማከናወን፣

- የሕዝብና ቤት ቆጠራ፣ የግብርና ቆጠራና እንደዚሁም ሌሎች ጠቅላላ ቆጠራዎች ተግባራት ወቅታቸውን ጠብቆ ለማካሄድና በዚሁ መስክ ጥናትና ምርምር በተቀናጀ መልክ ለማካሄድ የሚያስችል አቅም መገንባት ናቸው።

3.2 <u>የ1993 ዕቅድ አፈጻጸም ስልቶች</u>

- የአገሪቷ የስታቲስቲክስ ሥራ ጥራትና ደረጃው የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ይችል ዘንድ የባለሥልጣኑ መ/ቤት አቅሙን ለማጎልበት ጥረት ማድረግ፣

- ከተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ጋር የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት በማጠናከር በተለይም ሕብረተሰቡ የስታቲስቲክስ መረጃ አስፈላጊነትና ጥቅም በሚገባ ተረድቶ ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ረገድ ትብብር እንዲያደርግ በተለያዩ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ተገቢውን ትምህርትና ቅስቀሳ ማድረግ፣

- የስታቲስቲክስ የአሠራር ዘዴን በማሻሻል የመረጃ መሰብሰብ፣ ቅንብርና ትንተና ሥራ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል ስለሚያስፈልግ በዚህ በኩል የሚመደብ ሠራተኛ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር እንዲሰለጥን ማድረግ፣

- የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከተለያዩ የውጭ አገር መንግሥታት፣ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር በቀጥታም ሆነ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት

በኩል ግንኙነት በመፍጠርና ብሉም በማጠናከር ጥናት ማካሄድ፣ የሥልጠናና የፋሲሊቲዎች ድጋፍ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ናቸው።

## 4. የ1993 ዕቅድ ይዘት

በ1993 የበጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም በመታቀፍና በተናጠል ሊጠኑ ከታቀዱት ጥናቶች በሙሉ አዲስና አገርአቀፍ ይዘት ያላቸው ጥናቶች ናቸው። በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም በርካታ ጥናቶች የተካተቱ ሲሆን ይህም የባለሥልጣኑ መ/ቤት ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ሎጀስቲክስና የፋይናንስ አቅም በማቀናጀት በአንድ ወቅት ሁለት ወይም ከዛ በላይ ጥናቶችን በማካሄድና ሌሎች ጥናቶችን በማከታተል ለማከናወን የታቀደ ነው። መ/ቤቱ በተጠቀሰው በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የታቀፉ አሥራ አንድ ልዩ ልዩ ጥናቶችና የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት በከብት እርቢ አካባቢ፣ በትላልቅ የመንግሥትና የግል የንግድ እርሻዎች እንደዚሁም በከተሞች ለማካሄድ አቅዷል። በመሆኑም በ1993 ዓ.ም የስታቲስቲክስ ፕሮግራም መሠረት በዕቅድ ዓመቱ መጠናት ያለባቸው ጥናቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው።

<u>በ1993 ለማካሄድ የታቀዱ ጥናቶች</u>

ሀ. <u>ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም</u>

1 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት
2 የሰብል ምርት ጥናት
3 የመሬት አጠቃቀም ጥናት
4 የቤት እንስሳት፣ የዶሮና የንብ ጥናት
5 የግብርና ግብአቶችና አሠራር(Practices) ጥናት
6 የመንግሥትና እርሻዎች ጥናት
7 የመካከለኛና የትላልቅ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት
8 የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት
9 የዕቃዎችና አገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት
10 የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ናሙና ጥናት
11 የሕፃናት በሥራ ሁኔታ ጥናት ( Survey of child labor) በዓለም ዓቀፍ ሠራተኞች ድርጅት ( ILO) ድጋፍና ትብብር የሚሠራ ናቸው።

ለ. <u>አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት</u>

1. በናሙና በሚመረጡ ከተሞች የሚካሄድ የሙከራ ጥናት
2. በከብት እርቢ አካባቢዎች የሚካሄድ የሙከራ ጥናት
3. የመንግሥት፣ የማህበራትና ሰፋፊ እርሻዎች የሙከራ ጥናቶ፣
4. ሌሎች የዝግጅት ሥራዎች::

## 5. <u>የ1993 ካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ</u>

### 5.1 <u>የካፒታል በጀት ፍላጎት</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1993 በጀት ዓመት ለሚያካሂዳቸው የተለያዩ ጥናቶች ማስፈጸሚያ ማለትም ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም 30.71 ሚሊዮን ብር ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት 15.47 ሚሊዮን በጠቅላላ 46.18 ሚሊዮን ብር የተጠየቀ በጀት ነው::

### 5.2 <u>የካፒታል በጀት ፍላጎት መግለጫ</u>

በ1993 ሊጠኑ በዕቅድ የተያዙ ጥናቶች ዓይነትና ብዛት የተወሰነው በአብዛኛው በመ/ቤቱ የአፈጻጸም አቅም ላይ የተመሠረተ ሲሆን በሂደት ግን የመ/ቤቱ አቅም ሲጎለብት የጥናቶቹ ዓይነት፣ ብዛትና ይዘት ተሻሽሎ እንደሚለወጥ ይገመታል:: በዚሁ መሠረት የ1993 የካፒታል በጀት ፍላጎት በዝርዝር የተሰላው ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማካተት ነው::

5.2.1 መረጃ የሚሰበሰብባቸው የቆጠራ ቦታዎች ብዛት በገጠር 1450 ሲሆን በተጨማሪም በ45 ከተሞች የዋጋዎችና የቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃዎች ይሰበሰባሉ:: እንደዚሁም ከማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናቱ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መረጃዎች ይሰበሰባሉ::

5.2.2 ገጠርን በተመለከተ ሪፓርት የሚወጣው በዞን ደረጃ ሲሆን ከተማን በተመለከተ ደግሞ በያንዳንዱ የክልል ከተማ፣ እንደዚሁም በያንዳንዱ ከመቶ ሺህ ሕዝብ በላይ ነዋሪ ላለው ከተማ በየክልሉ "ከተማ ክፍል"(regional urban) ደረጃ ነው::

5.2.3 በደመወዝ የወጪ አርዕስት የተጠቀሰው የሰው ኃይል በሙሉ በኮንትራት ቅጥር የሚሟላ እንጂ መደበኛ ወይም ቋሚ ሠራተኞችን አይጨምርም። የቋሚ ሠራተኞች ወጪ በቁጥጥርና በሥልጠና ወቅት ለሚሳተፉት የሚከፈላቸው የውሎ አበል እንዳስፈላጊነቱ ለሌሎች ወጪዎች በፕሮጀክቱ ሂሣብ የሚሸፈን ይሆናል።

5.2.4 ለወጪ ቅነሳና የሰው ኃይል ጉልበት በአግባቡ ለመጠቀም አንድ መረጃ ሰብሳቢ በአንድ ምድብ የሥራ ቦታ ( የቆጠራ ቦታ) ከሁለት ወይም ከሦስት ጥናቶች በላይ የተዘጋጁትን መጠይቆችን በአንድ ወቅት ወይም በቅደም ተከተል መረጃዎችን እንዲሰበስብ ይደረጋል። እንደዚሁም ኤዲተሮችና ኢንኮደሮች በሚወጣላቸው ፕሮግራም መሠረት በተናጠል ወይም በጋራ የሁሉንም ጥናቶች መረጃዎች ኤዲትና ኮድ በማድረግ ከዛም በዳታ ኢንኮደሮች አማካይነት መረጃዎች ወደ ኮምፕዩተር ውስጥ ያስገባሉ። በተመሳሳይ ሁኔታም በሥልጠናና በመስክ ቁጥጥር ወቅት ለሁሉም ጥናቶች የመስክ መኪናዎች አጠቃቀም በጋራ ይሆናል። እንደዚሁም ከዋናው መ/ቤት የኤክስፐርት ተቆጣጣሪዎች ስምሪት በቅንጅት ለገጠርና ለከተማ ጥናቶች ይሆናል።

5.2.5 በጽሕፈት መሣሪያዎችና በሕትመት የወጪ ርዕስ የተገለጸው አኃዝ ለጥናቶቹ የሚያስፈልገውን የሚያጠቃልል ሲሆን በዝርዝር ሲገለጽ ለጥናቶቹ ለሚሰማራው የሰው ኃይል የሚያስፈልገው የጽሕፈት መሣሪያዎች ማለትም እርሳስ፣ መቅረጫ፣ ላፒስ፣ እስክሪፕቶ፣ ማስታወሻ ደብተር፣ ከላሰር... ወዘተ ሲሆኑ በሕትመት ወጪ የሚጠቃለሉ ደግሞ ለመመሪያዎች፣ ለተለያዩ መጠይቆችና ቅጾች እንደዚሁም ለሪፖርቶች ዝግጅት የሚሆን የወረቀት ብዛትና ኬሚካሎች የሚገዙበት ዋጋ ተተምኖ የተሰላ ነው።

"ሌሎች ወጪዎች" በሚል ርዕስ የተመለከቱት በየዕቅድ ዘመናቱ ከሚያካሂዳቸው ፕሮጀክቶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው የቀረቡ ናቸው። እነዚህም

ሀ. <u>የሥልጠና አዳራሾች ኪራይ</u>

የተለያዩ ጥናቶችን አስመልክቶ በሥራው ለሚሠማሩ ሠራተኞች በተለይም ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለተቆጣጣሪዎች በመጠይቆቹ ይዘትና በመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ላይ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ። የቅ/ጽ/ቤቶች ደግሞ ያለውን

የሰው ኃይልና ሎጂስቲክስ የሚያስተናግድ በቂ ቢሮዎች እንኳን የሌላቸው ሲሆን የስብሰባና የሥልጠና አዳራሾችን ግን ከትምህርት ቤቶችና ከሌሎች መ/ቤቶች በትብብርና በኪራይ መልክ ተፈልጎ ሲገለገሉ ቆይተዋል። ይህንን ቋሚ ችግር ለማቃለል በቀጣዮቹ ዓመታት በጀት ተጠይቆ የቅ/ጽ/ቤቶች የቢሮና ሁለ ገብ አዳራሾች ፍላጎት በግንባታ ለማሟላት እስኪሞከር ድረስ በአማካይ 25 አዳራሾችን በቀን ሂሳብ ለመከራየት እንዲቻል ታስቦ የተጠየቀ በጀት ነው።

ለ. <u>የወባ ትንኝ መከላከያ መረብ</u>

በገጠር ከተመረጡ 1450 የቆጠራ ቦታዎች መካከል ወደ 600 የሚጠጉ የቆጠራ ቦታዎች በወባማ አካባቢዎች ውስጥ እንደሚሆኑ ስለሚገመት በእነዚህ አካባቢዎች ተመድበው ለሚሠማሩ ሠራተኞች የወባ ትንኝ መከላከያ መረብ ቢሰጣቸው በጤና መታወክ መደበኛ ሥራቸውን በማከናወን ረገድ የሚደርሰውን ችግር በማስወገድ የመስክ ሠራተኞች የሚፈለግባቸውን ያህል የሥራ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ እና በሕይወት ሕልፈት ተጠቂ የሚሆኑትን ሠራተኞች ጉዳት ለመቀነስ ታስቦ የተጠየቀ በጀት ነው። ለምሳሌ በ1991 እና በ1992 ዓ.ም ብቻ ከወባ ጠንቅ ጋር በተያያዘ ስድስት ሠራተኞች የሕይወት ሕልፈት ደርሶባቸው የአደጋ ኢንሹራንስ ሽፋን ማግኘታቸው ይታወቃል።

ሐ. <u>ለአሳይታ፣ ጅጅጋና ባሕር ዳር ቅ/ጽ/ቤቶች</u>

የቢሮ ግንባታ ከ22ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል 7ቱ በመንግሥት ቤት በነጻ፣ 15ቱ ደግሞ ከግለሰብና ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር በዓመት ብር 100,692 ኪራይ እየተከፈለ ቢሆንም ከእነዚህ ውስጥ ከ3 ቅ/ጽ/ቤቶች በስተቀር ሌሎቹ የያዟቸው ቢሮዎች ብዛት ያላቸውን ሠራተኞችና ሎጂስቲክስ ለማስተናገድ ፈጽሞ አመቺ ሆኖ አልተገኘም። ይህም ችግር ወደፊት በሂደት ወጥነት ባለው መጠነኛ ግንባታ እስኪቃለል ድረስ ኪራይ በማፈላለግ ለመቆየት ቢታሰብም በተለይም በአሣይታ፣ በጅጅጋ፣ ባሕርዳርና በአሶሳ በኪራይ መልክም ቢሆን በቂ ቢሮዎች ለማግኘት ስላልተቻለ በእነዚህ አካባቢዎች ለሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች የግንባታ በጀት ተፈቅዶ ችግሩ ቢቃለል የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ታምኖበት ቀርቧል።

## መ. ለሠራተኞች የአደጋ ኢንሹራንስ

በሕዝብና ቤት ቁጠራዎች ወቅትና በተለያዩ ጊዜያት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በሥራ ላይ የሕይወትና የአካል ጉዳት ስለደረሰባቸው በዚሁ ተመክሮ በገጠር አካባቢ ተመድበው ለሚንቀሳቀሱ ሠራተኞች ብቻ የአደጋ ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ታምኖበት ባለፉት ሁለት ዓመታት ተግባራዊ ሆኖ ተጎጂ ሠራተኞች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በገጠር አካባቢ የሚሠማሩ ሠራተኞች በሙሉ የአደጋ ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ታስቦ የቀረበ በጀት ነው፡፡

## ሠ. በመያዣነት ( Retension) የቆየ ተከፋይ

ባለፉት ሁለት በጀት ዓመታት በተፈቀደ ካፒታል በጀት የቤተመጻሕፍት ሕንጻ ግንባታ ሲካሄድ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ለሕንጻ ተቋራጩ መከፈል ከሚገባው ገንዘብ የጠቅላላ ዋጋው 10% በመያዣነት እንዲቆይና ሥራው ተጠናቆ ርክክብ ሲደረግ የሚከፈለው ስለሆነ በ1993 በጀት ዓመት ውስጥ ተከፋይ ስለሚሆን በበጀት ተይዞ ቀርቧል፡፡

6. ## የ1993 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1993 በጀት ዓመት ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ብር 31,231,516 እንደዚሁም ለማብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ብር 27,013,555 በድምሩ ብር 58,245,071 ያስፈልጋል:: ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል::

6.1 ### ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የበጀት ፍላጎት ማጠቃለያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. | ለወደመወዝ | ብር | 7,747,632 |
| ለ. | ለውሎ አበል | ብር | 4,619,328 |
| ሐ. | ለሥልጠና | ብር | 1,518,656 |
| መ. | ለትራንስፖርትና ጥገና | ብር | 10,534,370 |
| ሠ. | ለጽሕፈት መሣሪያዎችና ሕትመት | ብር | 859,900 |
| ረ. | በገጠር ለሚሰማሩ ሠራተኞች ኢንሹራንስ | ብር | 576,000 |
| ሰ. | ለሥልጠና አዳራሾች ኪራይ | ብር | 150,000 |
| ሸ. | ለ15 ቅ/ጽ/ቤቶች የቢሮ ኪራይ | ብር | 113,652 |
| ቀ. | ለአራቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ቢሮ ማሠሪያ (ግምት) | ብር | 2,000,000 |
| በ. | ለሕንጻ ተቋራጭ የሚከፈል መያዣ | ብር | 130,000 |
| ተ. | ለወባ ትንኝ መከላከያ መረብ መግዣ | ብር | 72,000 |
| ቸ. | ለአሮጌና ለተበላሹ ዕቃዎች ማስጠገኛ | ብር | 50,000 |
| ነ. | የሒሣብ መኪና (calculator) መግዣ | ብር | 20,750 |
| | ድምር | ብር | 28,392,288 |
| | መጠባበቂያ ( 10%) | ብር | 2,839,229 |
| | ጠቅላላ ድምር | ብር | 31,231,516 |

# የ1993 በጀት ዓመት ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የካፒታል በጀት ፍላጎት

ሠንጠረዥ 1

| የወጪዎች ዝርዝር<br>በወጪ አርዕስት | የ ስ ታ ቲ ስ ቲ ክ ስ ጥ ና ቶ ች ዓ ይ ነ ት | | |
|---|---|---|---|
| | ገ ጠ ር | ከ ተ ማ | |
| | . የሰብል ትንበያ ጥናት<br>. የሰብል ምርት ጥናት<br>. የመሬት አጠቃቀም ጥናት<br>. የቤት እንስሳት፣ የዶሮና የንብ ጥናት<br>. የግብርና ግብአቶች አሠራር ጥናት<br>. የመንግሥትና የግል እርሻዎች ጥናት<br>. የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት<br>. የዕቃዎችና የአገል. የችርቻሮ ዋጋ ጥናት<br>. የቫይታል ምዝገባ የናሙና ጥናት<br>. የሕጻናት የሥራ ሁኔታ ጥናት * | . የመካከለኛና ትላልቅ ኢንድስትሪዎች ጥናት | . የዕቃዎችና የአገል.የችርቻሮ ዋጋ ጥናት<br>. የቫይታል ምዝገባ የናሙና ጥናት<br>. የኢንዴክሶች ዝግጅት |
| 1. ደ መ ወ ዝ | | | |
| . ለጀማሪ ፕሮፌሽናሎች | 66 x 710 x 12= 562,320 | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢ | 1182 x 347 x 12 = 4,921,848 | 108 x 347 x 3 = 112,428 | 79 x 347 x 12 = 316,464 |
| . ለመስክ ተቆጣጣሪዎች | 91 x 500 x 12 = 546,000 | 33 x 500 x 3 = 49,500 | 14 x 500 x 12 = 84,000 |
| . ለሾፌሮች | 186 x 285 x 12 = 636,120 | | |
| . ለኤዲተሮች | 17 x 420 x 12 = 85,680 | | |
| . ለዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች | 48 x 347 x 12 = 199,872 | | |
| . የፐርሶኔል ሠራተኞች | 24 x 600 x 12 = 172,800 | | |
| . ለቀን ሙያተኞች | 25 x 154 x 12 = 46,200 | | |
| . ለመካኒኮች | 2 x 600 x 12 = 14,4000 | | |
| ንዑስ ድምር | 7,185,240 | 161,928 | 400,464 |

* በዓለም አቀፍ ሠራተኞች ድርጅት ( ILO) ትብብርና ድጋፍ የሚሠራ

| | | | |
|---|---|---|---|
| II የሥልጠና ወጪ. | | | |
| ሀ/ 1. የማብርና ስታቲ. ጥናቶች | | | |
| 2. የዋጋዎች ጥናት | | | |
| 3. የቫይታል ምዝገባ ናሙና ጥናት | | | |
| በዋናው መ/ቤት | | | |
| . ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | 44 x 25 x 32 = 35,200 | | |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 22 x 25 x 18 = 9,900 | | |
| . ለዋናው መ/ቤት ኤክስፐርቶችና አሰልጣኞች የምግ አበል | 90 x 25 x 14 = 31,500 | | |
| በቅ/ጽ/ቤቶች | | | |
| . ወደ ቅ/ጽ/ቤት ለሚሰማሩ ኤክስፐርቶችና አሰልጣኞች | 90 x 35 x 32 = 100,800 | | |
| . ከኤክስፐርቶች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 22 x 35 x 18 = 13,860 | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች ውሎ አበል | 1733 x 35 x 20 =1,213,100 | | |
| . ለተቆጣጣሪዎች የምግ አበል | 337 x 35 x7 = 82,565 | | |
| ለ/ 1. የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱ.ጥናት | | | |
| . ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | | 44 x 9 x 32 = 12,672 | |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | | 22 x 9 x 18 = 3,564 | |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ለሚመጡ ተቆጣጣሪዎች | | 22 x 9 x 24 = 4,752 | |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ለሚመጡ መረጃ ሰብሳቢዎች | | 43 x 9 x 20 = 7,740 | |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚመደቡ ተቆጣጣሪዎችና አሰልጣኞች የምግ አበል | | 13 x 7 x 8 = 728 | |
| . የአ. አበባ ከተማ መረጃ ሰብሳቢዎች የምሳ አበል | | 65 x 7 x 5 = 2,275 | |
| ንዑስ ድምር | 1,486,925 | 31,731 | |

| III ውሎ አበል | | | |
|---|---|---|---|
| .ከዋናው መ/ቤት ለመስክ ግምገማ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች | 44 x 80 x 32 = 112,640 | 44 x 30 x 32 =42,240 | 44 x 30 x 32 = 42,240 |
| . ከግምገማ ባለሙያዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 22 x 80 x 18 = 31,680 | 22 x 30 x 18 =11,880 | 22 x 30 x 18 = 11,880 |
| . የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው የመስክ ጉብኝትና ቁጥጥር | 44 x 90 x 32 = 126,720 | - | |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 22 x 90 x 18 = 35,640 | - | |
| . ለመስክ ተቆጣጣሪዎች | 323 x 180 x 24 =1,395,360 | | |
| . ከመስክ ተቆጣጣሪዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 148 x 180 x 18 = 479,520 | | |
| . ለሂሣብ ሠራተኞች | 22 x 72 x 22 = 34,848 | | |
| . ለሜትር ኀታች | 1450x80x10=1,160,000 | | |
| . ለዋጋ ጥናት መረጃ ሰብሳቢዎች ረዳት | 540 x 52 x 10 = 280,800 | | 45 x 52 x 10 = 23,400 |
| . ለዋጋ መረጃ ሰብሳቢዎች የምግ አበል | 540 x 52 x 5 = 140,400 | | 45 x 52 x 5 = 11,700 |
| . ለቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃ ሰብሳቢ ጠቋሚ | 56 x 12 x 30 = 20,160 | | 24 x 12 x 30 = 8,640 |
| . ለኢንዱስትሪ ጥናት ለሚሰማሩ | | | |
| መረጃ ሰብሳቢዎች የምግ አበል | | 108 x 60 x 5 = 32,400 | |
| . ለተቆጣጣሪዎች የምግ አበል | | 33 x 60 x 7 = 13,860 | |
| . ለኢንዱስትሪ ጥናት ለሚሰማሩ | | | |
| ሾፌሮች የምግ አበል | | 25 x 60 x 4.50 = 6,750 | |
| . ለመ.ሰብሳቢዎች የመጠለያ አበል | 1450 x 12 x 30 = 522,000 | | |
| . ለመንገድ መሪዎች | 1450 x 5 x 10 = 72,500 | | 69 x 3 x10 = 2,070 |
| | | | |
| **ንዑስ ድምር** | **4,412,268** | **107,130** | **99,930** |

| | | | |
|---|---|---|---|
| IV ትራንስፖርትና ጥገና | | | |
| . ለመስክ ቁጥጥር የሚያስፈልግ ነዳጅ | 148 x 180 x 30 x 3 = 2,397,600 | 44 x 90 x25 x 3 = 297,000 | |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚሰማሩ ነዳጅ | 22 x 90 x 30 x3 = 178,200 | | |
| . በሥልጠና ወቅት የሚያስፈልጉ ነዳጅ | 22 x 35 x 5 x 3 = 11,550 | 22 x 30 x5 x3 = 9,900 | |
| . ለአሮጌ መኪናዎች ጥገና | 72 x 3000 x 12= 2,592,000 | | |
| . ለአዲስ መኪናዎች ጥገና | 120 x 2000x12= 2,880,000 | | |
| . ለኢንሹራንስ | 192x 1980 = 380,160 | | |
| . ለጎማ | 192x 10 x 600 = 1,152,000 | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች ትራንስፖርት | 1595 x 15 x 4 = 95,700 | | |
| . ለኢንዱ. መ/ሰብሳቢዎች የትራን. አበል | | 108 x 60 x 7 = 45,360 | |
| . ለመስክ ተቆጣጣሪዎች የበቅሎ ኪራይ | 323 x 300 = 96,900 | | |
| . ለስልክ፣ ለፖስታ፣ ለፋክስና ለቴሌግራም | 1500 x 22 x 12 = 396,000 | 2,000 | |
| **ንዑስ ድምር** | **10,180,110** | **354,260** | |
| V. የጽሕፈት መሣሪያዎችና ሕትመት | | | |
| ሀ/ አላቂ የጽሕፈት መሣሪያዎች | 72,400 | | |
| ለ/የሕትመት ወረቀት፣ ኬሚካልና ቀለም | 787,500 | | |
| **ንዑስ ድምር** | **859,900** | | |
| VI. ሌሎች ወጪዎች | | | |
| ሀ/ለስልጠና አዳራሾች ኪራይ | **25 x 30 x 200 = 150,000** | | |
| ለ/ የወባ ትንኝ መከላከያ መረብ | **600x 120 = 72,000** | | |
| ሐ/ ለ15 ቅ/ጽ/ቤቶች ቢሮ ኪራይ | | 113,652 | |
| መ/ በቂ ቢሮዎች በኪራይ ማግኘት ባልተቻለባቸው | | | |
| ቅ/ጽ/ቤቶች ቢሮ ማስሪያ/አሳይታ፣ ጂጂጋና ባህርዳር አሶሳ | | 4 x 500,000 = 2,000,000 | |
| ሠ/ በገጠር አካባቢዎች ተመድበው ለሚንቀሳቀሱ ሠራተኞች የአደጋ ኢንሹራንስ | **2400 x 240 = 576,000** | | |
| ረ ለቤተ መጻሕፍት ሕንጻ ግንባታ ለተቋራጩ መክፈል የሚገባው | | | |
| 10%በመያዣነት የቆጠና (ከ)ከበ ተጠቃሎ ሲፈፀም ተከፋይ የሚሆን | | **130,000** | |
| መ/ አሮጌና የተበላሹ ዕቃዎች ማስጠገኛ | **50,000** | | |
| ሠ/ የሒሣብ መኪና (Calculator) | | **83 x 250 = 20,750** | |
| **ንዑስ ድምር** | **848,000** | **2,264,402** | - |
| **ድምር** | **24,972,443** | **2,919,451** | **500,394** |
| **መጠባበቂያ (10 %)** | **2,497,244** | **291,945** | **50,039** |
| **ጠቅላላ ድምር** | **27,469,687** | **3,211,396** | **550,433** |

**31,231,516**

## 6.2 ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናትና የዝግጅት ሥራዎች

## የበጀት ፍላጎት ማጠቃለያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. | ለደመወዝ | ብር | 265,030 |
| ለ. | ለሥልጠና | ብር | 123,316 |
| ሐ. | ለውሎ አበል | ብር | 361,818 |
| መ. | ለትራንስፓርት ወጪ | ብር | 90,680 |
| ሠ. | በከብት አርቢ አካባቢዎችና በገጠር ለሚንቀሳቀሱ ሠራተኞች የአደጋ ኢንሹራንስ | ብር | 22,600 |
| ረ. | ለጽሕፈት መሣሪያዎችና ሕትመት (ለዋናው ቆጠራ ጨምሮ) | ብር | 1,579,636 |
| ሰ. | ለመስክ መኪናዎች ግዢ | ብር | 6,506,528 |
| ሸ. | ለመኪናዎች ቀረጥ | ብር | 5,395,606 |
| ቀ. | በዋናው ቆጠራ ሥራ ለሚሠማሩ ሠራተኞች ሥልጠናና ስምሪት | ብር | 10,042,076 |
| በ. | በእርዳታ ለተገኙ መኪናዎች ለልዩ ልዩ የአገር ውስጥ ወጪዎች መሸፈኛ | ብር | 170,487 |
| | ድምር | ብር | 24,557,777 |
| | መጠባበቂያ(10%) | ብር | 2,455,778 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **ብር** | **27,013,555** |

## ለግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናትና የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የበጀት ፍላጎት

ሠንጠረዥ 2

| የወጪዎች ዝርዝር በወጪ አርዕስት | የ ሙ ከ ራ ጥ ና ቶ ች ዓ ይ ነ ት | | |
|---|---|---|---|
| | በናሙና በሚመረጡ ከተሞች የሚካሄድ የሙከራ ጥናት | በከብት አርቢ አካባቢዎች የሚካሄድ የሙከራ ጥናት | የመንግሥት፣የማሕበራትና የግል ሰፋፊ እርሻዎች የሙከራ ቆጠራ |
| **1. ደ መ ወ ዝ** | | | |
| . መረጃ ሰብሳቢዎች | 70 x 285 x 4 = 79,800 | 114 x 285 x 3 = 97,470 | 68 x 285 x 2 = 38,760 |
| . ለተቆጣጣሪዎች | 14 x 500 x 4 = 28,000 | 14 x 500 x 3 = 21,000 | - |
| **ንዑስ ድምር** | **107,800** | **118,470** | **38,760** |
| **II የሥልጠና ወጪ** | | | |
| . አሰልጣኞች የምሣ አበል | 4 x 20 x 14 = 1,120 | 6 x 20 x 14 = 1,680 | 2 x 15 x 14 = 420 |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች ውሎ አበል | 70 x 24 x 18 = 30,240 | 114 x 24 x 18 = 49,248 | 68 x 20 x 18 = 24,480 |
| . ለተቆጣጣሪዎች ውሎ አበል | 14 x 24 x 24 = 8,064 | 14 x 24 x 24 = 8,064 | |
| **ንዑስ ድምር** | **39,424** | **58,992** | **24,900** |
| **III ውሎ አበል ወጪ** | | | |
| . ከዋናው መ/ቤት ለመስክ ግምገማ ለሚሠማሩ ባለሙያዎች | 8 x 30 x 32 = 7,680 | 8 x 30 x 44.80 = 10,752 | 6 x 15 x 32 = 2,880 |
| . ከገምጋሚ ባለሙያዎች ጋር ለሚሠማሩ ሾፌሮች | 4 x 30 x 18 = 2,160 | 4 x 30 x 25.20= 3,024 | 3 x 15 x 18 = 810 |
| . ለመስክ ተቆጣጣሪዎች | 14 x 30 x 24 = 10 , 080 | 14 x 30 x 33.60 = 14,112 | - |
| . ከመስክ ተቆጣጣሪዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 3 x 30 x 18 = 1, 620 | 3 x 30 x 25.20 = 2,268 | - |
| . ለመንገድ መሪዎችና አስተርጓሚዎች | - | 4 x 60 x 44.80= 306,432 | - |
| | | | |
| **ንዑስ ድምር** | **21,540** | **336,588** | **3,690** |

| | | | |
|---|---|---|---|
| IV የትራንስፖርት ወጪ *  | | | |
| . ለመኪናዎች ነዳጅ | 7 x 60 x 20 x 3 = 25,200 | 7 x 60 x 30 x 3 = 37,800 | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች የትራንስፖርት ወጪ | 70 x 30 x 2 = 4,200 | 114 x 50 x 2 = 11,400 | 68 x 30 x 2 = 4,080 |
| . ለአየር /አይሮፕላን ትራንስፖርት | - | 8 x 500 x 2 = 8,000 | - |
| **ንዑስ ድምር** | **29,400** | **57,200** | **4,080** |
| **V ሌሎች ወጪዎች** | | | |
| . ለጽሕፈት መሣሪያዎችና ሕትመት | 14,500 | 17,000 | 7,500 |
| . በከብት አርቢ አካባቢዎችና በገጠር ለሚመደቡ ሠራተኞች የአደጋ ኢንሹራንስ | - | 143 x 120 = 17,160 | 68 x 80 = 5,440 |
| . ለመስክ መኪናዎች ግዢ (CIF ዋጋና ሌሎች የአገር ውስጥ ወጪዎች ጨምሮ) | 28 x 232,376 = 6,506,528 | | |
| . ለመኪናዎች ቀረጥ ( Customs+Sales +Sur Taxes) | 28 x 151,970= 4,255,160 | | |
| . በ1992 በጀት ዓመት በተፈቀደ በጀት ለተገዙ 22 መኪናዎች የሚያስፈልግ ተጨማሪ ቀረጥ | 60,752 | | |
| . በእርዳታ ለተገኙ 9 መኪናዎች ቀረጥ | 9 x 119,966 = 1,079,694 | | |
| . በእርዳታ ለተገኙ 9 መኪናዎች ልዩ ልዩ የአገር ውስጥ ወጪዎች መሸፈኛ | 9 x 18,943 = 170,487 | | |
| . ለዋናው ቆጠራ ማስፈፀሚያ ለጽሕፈት መሣሪያዎች ግዢና እንዲሁም ለመጠይቆች መመሪያዎችና ለተለያዩ ዶክመንቶች ሕትመትና ሥርጭት | 1,540,636 | | |
| . በዋናው ቆጠራ ለሚሠማሩ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | 10,042,076 | | |
| **ንዑስ ድምር** | **23,669,833** | **34,160** | **12,940** |
| **ድምር** | **23,867,997** | **605,410** | **84,370** |
| **መጠባበቂያ (10%)** | **2,386,800** | **60,541** | **8,437** |
| **ጠቅላላ ድምር** | **26,254,797** | **665,951** | **92,807** |
| | **27,013,555** | | |

* የመኪናዎች የጥገና፣ የኢንሹራንስ፣ የጎማ ወጪና የሾፌሮች ደመወዝ በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ውስጥ ስለተያዘ በዚህ ጥናት ለሚሠማሩ መኪናዎች የበጀት ጥያቄ አልቀረበበትም፡፡

## የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናትና የቅድመ - ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተ

በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1993 በጀት ዓመት ውስጥ አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ ለማካሄድ ታቅዶ ካለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ ቆጠራውን ለማካሄድ የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችና የሙከራ ቆጠራ ጥናት በአብዛኛው የተጠናቀቀ ቢሆንም በተለይም በከብት እርቢ አካባቢዎች ቆጠራው የሚካሄድበት ዘዴና ወቅት የተለያየ ከመሆኑም በላይ መርጦ ለመወሰንና ተግባራዊ ለማድረግ በሙከራ ደረጃ በ1993 ዓ.ም በስፋት የሚካሄድ ቀሪ ሥራዎች እንደሚኖሩ ታቅዷል፡፡ እንደዚሁም የግብርና ቆጠራው አካል የሚሆነው ሰፋፊ የመንግሥት፣ የግል የንግድ፣ የሕብረት... ወዘተ እርሻዎች ስርጭትና አጠቃላይ ሁኔታ በቅድሚያ በሙከራ መልክ ተጠንቶ መታወቅ ስለሚኖርበት በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሚከናወን ተግባር ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በናሙና በተረመጡ ከተሞች የሙከራ ቆጠራ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

በ1993 በጀት ዓመት ለማካሄድ ለታቀደው አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ ማስፈፀሚያ ወደ 111 ሚሊዮን ብር የሚገመት የካፒታል በጀት እንደሚያስፈልገውና ከዚሁ የሚታሰብ ሆኖ በቆጠራው ሥራ ለሚሰማሩት 14,000 ሠራተኞች የሥልጠና ወጪ 10 ሚሊዮን ብር ገደማ፣ እንደዚሁም ለጽሕፈት መሣሪያዎች ግዢና ለቆጠራው የሚያስፈልጉ ብዛት ያላቸው ዶኩመንቶች በወቅቱ ለማሳተምና ለማሠራጨት እንዲቻል የተጠየቀው ተጨማሪ በጀት በወቅቱ ተፈቅዶ ሊገኝ ባለመቻሉ፣ የቆጠራው ማስፈጸሚያ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ወጥቶ ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ መቋቋም የሚገባቸው ኮሚሽኖችና የኮሚሽን ጽ/ቤቶች እስካሁን ባለመቋቋማቸውና ባለመደራጀታቸው ቆጠራው በተያዘለት ዕቅድ መሠረት በ1993 በጀት ዓመት ለማካሄድ እንደማይቻል ግንዛቤ ለማግኘት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ለበጀት ዓመቱ ለቀረበው የካፒታል በጀት ዝግጅት ጥሪ በወቅቱ ምላሽ ለመስጠት ( እስከ መጋቢት 30/1992 ዓ.ም ድረስ) እንዲቻል ለዋናው ቆጠራ የሚያስፈልገው በጀት በወቅቱ ባለመፈቀዱና ቅድመ - ሁኔታዎች ባለመመቻቸታቸው ቆጠራው እንደሚሸጋሸግ ታሳቢ ተደርጎ ከመደበኛው ብሔራዊ ሰርቬይ ፕሮግራም በተጨማሪ ከላይ እንደተጠቀሰው የሙከራ ጥናቶችና ሌሎች ቀሪ የዝግጅት ሥራዎች በ1993 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዷል፡፡ ለዚህም የካፒታል በጀት ፍላጎት በሠንጠረዥ 2 ተተምኖ ቀርቧል፡፡

## 7. የ1993 ጥናቶች ግብና መግለጫ

### 7.1 የ1993 ጥናቶች ግብ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1993 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም በመታቀፍ አሥር የተለያዩ ጥናቶችንና የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናትን ጨምሮ በገጠርና በከተማ ለማካሄድ አቅዷል።

በብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም አማካይነት የሰው ኃይል፣ ሎጀስቲክስና በጀትን በማቀናጀት ከሚካሄዱት ጥናቶች መሐል ከዋጋ ጥናት በስተቀር ሁሉም በተያዘላቸው በጀት ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቁ ይሆናሉ። የዋጋ ጥናትን በተመለከተ ግን ጥናቱ የሚጀመረው በመስከረም ወር በመሆኑ የሐምሌና የነሐሴ ወራት መረጃዎች የሚሰበሰቡት፣ የሚጠናቀሩትና ሪፖርታቸው የሚዘጋጀው በ1994 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው።

### 7.2. የ1993 ጥናቶች ዝርዝር መግለጫ

#### 7.2.1 የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

ሀ. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ዓላማዎች

የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ የሀገሪቱን ክልሎች በሙሉ በሚሸፍኑና በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የሚካሄድ ሲሆን የጥናቱ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

– በምርት ዓመቱ ሊገኝ የሚችለውን ምርት በመገምገምና በምርት ዘመኑ ሊመረት የሚችለውን ጠቅላላ የምርት መጠን (Total Production Forecast) ከወዲሁ በመገመት ወደፊት በሀገሪቱ ሊመረት የሚችለውን የምርት መጠን ለመተንበይ፣

- በምርት ዓመቱ ትርፍ ሊያመርቱ የሚችሉትንና የምርት እጥረት የሚያጋጥማቸውን ክልሎችና ዞኖች መለየት የሚያስችሉ የትንበያ መረጃዎችን መሰብሰብ ናቸው::

- <u>በሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

ከላይ የተዘረዘሩትን የጥናቱን ዓላማዎች ለማሟላት የሚከተሉት የመረጃ ዓይነቶች በተጨባጭና ( Objective) በቃለመጠይቅ ( Subjective) የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች በመጠቀም ጥናቱ ከሚካሄድባቸው የቆጠራ ቦታዎች ይሰበሰባሉ:: ከነዚህም መሐል:-

- የታረሰ መሬት ስፋት
- የሚጠበቀው የምርታማነት ለውጥ ከአለፈው ዓመት ምርት በሰብል ዓይነት ጋር ሲነፃፀር በመቶኛ ናቸው::

ለ. <u>የግብርና ናሙና ጥናት</u>

- <u>የግብርና ናሙና ጥናት ዓላማዎች</u>

ሀገሪቱ በየዓመቱ በግብርና ክፍለኢኮኖሚ ለምታዘጋጀው የአጭር፣ የመካከለኛና የረዢም ጊዜ ፓሊሲ እንደዚሁም የልማት ዕቅዶች ጥናት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው::

- በሀገሪቱ በዓመቱ የተመረተውን አጠቃላይ የሰብል ምርት መጠን ለማወቅ፣ በክልሎችና በዞኖች ደረጃ ያለውን የምርት ሁኔታ ለማወቅ፣ ለማወዳደርና ለማነፃፀር የሚያስችሉ መረጃዎች ለማግኘት፣

- በአንድ ሄክታር ላይ የሚገኘው ምርትና ምርታማነት ምን ያህል እንደሆነ እንደዚሁም በክልሎችና በዞኖች መሐል ያለውን የምርትና ምርታማነት ለማወዳደርና ለማነፃፀር የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት፣

- ከዓመት ወደዓመት በሀገር ደረጃ የታረሰ መሬት ስፋትና ያለውን የምርት መጠን በዋናው መኸርና በበልግ በመለየት በሰብል ዓይነት የታየውን ለውጥ ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎች ለማግኘት፣

- የእርሻ ሥራን አጠቃላይ ሁኔታ ማለትም ጥቅም ላይ የዋለ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና የፀረ-ሰብል መድኃኒት ዓይነት እንደዚሁም የመስኖ አጠቃቀም... ወዘተ ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት፣

- በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የመሬት አጠቃቀም ማለትም በሰብል ስለተያዘ መሬት፣ እጻሪ መሬት፣ በግጦሽ የተያዘ መሬት፣ በደን የተሸፈነ መሬት፣ ... ወዘተ የሚያሳዩ መረጃዎች ለማግኘት፣

- በሀገሪቱ ያሉትን የቤት እንስሳትን በተመለከተ ብዛታቸውን በዓይነት፣ በዕድሜና በፆታ እንደዚሁም ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ ለመገምገም የሚያበቁ መረጃዎችን ለማግኘት ናቸው።

- <u>በግብርና ናሙና ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

የዚህ ጥናት የዋናው መኸር ወቅት መረጃ ( የሰብል ምርት ግብአቶች ጨምሮ) ከመስከረም ወር መጀመሪያ እስከ የካቲት ወር መጨረሻ ድረስ የሚሰበሰብ ሲሆን የበልግ ወቅት መረጃ ደግሞ በግንቦት ወር ውስጥ ይሰበሰባል። የዓመቱ የግብርና ጥናት አካል የሆኑት የቤት እንስሳት፣ ዶሮና ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛት የሚያሳይ መረጃም ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በየካቲት ወር ውስጥ ተሰብስቧል። በንዑስ ጥናቶች አማካይነት ከሚሰበሰቡት መረጃዎች መሐል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- የታረሰ መሬት ስፋትና አማካይ የምርት መጠን በሰብል ዓይነት፣
- የዘር ዓይነት አጠቃቀም፣ የማዳበሪያ አጠቃቀም በዓይነት፣ በመጠንና በዋጋ፣ የፀረ -ሰብል ተባይና አረም ማጥፊያ አጠቃቀምና የቋሚ ሰብል እግር ብዛት፣
- የቤት እንስሳትና የዶሮ ብዛት በዓይነት፣ በዕድሜ፣ በፆታና በሚሰጡት የጥቅም ዓይነት፣
- የንብ ቀፎዎች ዓይነት፣ ብዛትና የማር ምርት መጠን የሚያሳዩ መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

7.2.2 <u>የአምራቾች የዋጋ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

የዋጋ ጥናት በየወሩ በገጠርና በከተማ ይካሄዳል:: በዚህ ጥናት አማካይነት የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋ መረጃዎች ይሰበሰባሉ:: እነዚህም መረጃዎች መሠረት ያደረገ በየወሩ በአገር አቀፍ፣ በገጠርና በከተማ እንደዚሁም በአዲስ አበባ የዋጋ እንደክሶች ይዘጋጃሉ::

- <u>የአምራቾች ዋጋ ጥናት ዓላማዎች</u>

የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ አበይት ዓላማዎች፣

- ፓሊሲ አውጪዎች ስለእርሻ ውጤቶች ምርትና ሥርጭት አስመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚረዱ መረጃዎች፣
- ገበሬዎች በአምራቾች ደረጃ ለእርሻ ውጤቶች የሚያስከፍሉትን ዋጋ መጠን ለማጥናት መሠረት የሆኑ መረጃዎች፣
- የምርት ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ውጤትን ለማስላት የሚረዱ እንደዚሁም በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማጥናት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎች፣
- የእርሻ ውጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋን የምርት መጠን መመዘኛ ኢንዴክሶችን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸው::

- <u>በአምራቾች ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

ለአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የግብርና ውጤቾች የአምራች ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የእህል፣ የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፦ የቅመማቅመም፣ የወተትና የወተት ተዋፅኦ፣ እንቁላል፣ የቁም ከብቶች፣... ወዘተ የዋጋ መረጃዎች ይሰበሰባሉ::

7.2.3 <u>የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት፣</u>

- <u>የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ዓላማዎች</u>

የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገጠርና በከተማ በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማዎች፦

- የችርቻሮ ዋጋ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማወቅ፣
- በተለያዩ የሥርጭት ደረጃዎች መካከል ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማወቅ፣
- በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለመገምገም፣
- ለቤተሰብ ፍጆታ የዋሉትን ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ለመተመን፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ምርትና ስርጭት በሚመለከት ፓሊሲ አውጪዎች ውሳኔ ለመድረስ የሚያስችሉ መነሻ መረጃዎች ለማግኘት፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ውጤትን ለማስላት እንደዚሁም የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት የሚያስችሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸው።

- <u>በችርቻሮ ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

ለችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገጠርና በከተማ ከተመረጡ የቆራ ቦታዎች በዋና ዋና የመገበያያ ሥፍራዎች የእርሻና የኢንዱስትሪ ውጤቶች ከግል ነጋዴዎች የችርቻሮ ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም፡-

የምግብ፣ የመጠጥ፣ የትምባሆ፣ የልብስ የጫማ፣ የሕንፃ መሣሪያዎች፣ የቤት መገልገያ ዕቃዎች፣ የሕክምና መድኃኒት፣ የመጓጓዣ፣ የትምህርት፣ የመዝናኛ፣ የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎች፣ የሆቴል ምግብና አልጋ... ወዘተ የዋጋ መረጃዎች ናቸው።

## 7.2.4 <u>የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ የናሙና ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

ሕዝብ-ነክ መረጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች የሚሰበሰቡ ሲሆን ከእነዚህ ዘዴዎች አንዱ በቋሚነት ምዝገባ ( Vital Reqistration) በማካሄድ ነው። በዚህ መረጃ የመሰብሰብ ዘዴ በሕብረተሰቡ ውስጥ ስለተከሰተው ሁኔታ እንበል የልደት፡-የሞት፣የጋብቻ፣የፍቺ እና የፍልሰት መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

- <u>የቫይታል ስታቲስቲክስ የናሙና ጥናት ዓላማዎች</u>

የጥናቱ ዓላማዎች በርካታ ሲሆኑ ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚቋቋመው በቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች በቅድሚያ ለማወቅ፣

- ምዝገባው ከሕግና አስተዳደር አንፃር እንደዚሁም በመረጃ ማቀናጀትና በሜቶዶሎጂ ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማወቅ፣

- የሕብረተሰቡ የምዝገባው አስፈላጊነትና ጥቅም እንዲረዳ ለማድረግ፣
- የሕዝቡን የዖታ፡- የዕድሜና የጋብቻ ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎች በመሰብሰብ የየዓመቱን የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ፣ የፍቺና የፍልሰት መጠን ለማጥናት፣

- ከቫይታል ምዝገባ በተጨማሪ ወደፊት የቫይታል ምዝገባ ሥርዓት በማያቋርጥ ሁኔታ (Continuous Registration) የሚቋቋምበትን መንገድ ለማጥናት፣ ... ወዘተ ናቸው።

- <u>በቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ የናሙና ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

በዚህ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።
- የሕዝቡን የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ፣ የፍቺና የፍልሰት መረጃዎች፣
- ከጥናቱ ጋር አግባብነት ያላቸው የዲሞግራፊ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

### 7.2.5 <u>የትላልቅና መካከለኛ የማመረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

በዚህ ጥናት አሥርና ከአሥር በላይ ሠራተኞች ከሚያሰማሩ፣ በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ካላቸው፣ አብዛኛው ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን ከሚያመርቱ ፋብሪካዎች ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡ ሲሆን ጥናቱ የሚካሄደውም በከተማዎች ክልል ነው።

- <u>የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ዓላማ</u>

የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት አበይት አላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የዘርፉን ዕድገት በሚመለከት የኢኮኖሚ ፖሊሲና የልማት ዕቅድ አውጪዎች እንደዚሁም ተመራማሪዎች በመነሻነት የሚጠቀሙበት ስታቲስቲካዊ መረጃ በኢንዱስትሪና በባለቤትነት ዓይነት ለማቅረብ፣

- ዘርፉ ያሰማራውን የሰው ኃይልና የምርት መጠን ለማወቅና ለሀገር ሀብት ውጤት የሚያበረክተውን ድርሻ ለማስላት አስፈላጊ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማግኘት፣

- ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከግብርናው ጋር ያለውን መስተጋብር እንዲሁም ከውጭ ጥሬ ዕቃዎችን በማስገባት በኩል ያለውን ድርሻ ለመገመት የሚያስችሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በዝርዝር መሰብሰብ ናቸው።

- <u>የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናትና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት የሚከተሉት ናቸው። እነዚህም:-

- የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም፣
- የተከፈለ ካፒታል መጠን ( Paid -up Capital) ፣
- የሠራተኞች ብዛት፥ ደመወዝና ምንዳ ፣
- የምርት መጠንና ዋጋ፥
- የጥሬ ዕቃ ፍጆታ ፣
- ልዩ ልዩ ከማምረት ይዘት ጋር የተዛመዱና ያልተዛመዱ ወጪዎች ፣
- የቋሚ ንብረት ዓይነትና በቋሚ ንብረት ላይ የተደረገ የመዋዕለ ንዋይ መጠን ፣
- የማምረት ችሎታ፣ ... ወዘተ አመልካች መረጃዎችን ይሰበሰባሉ።

### 7.2.6 የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ለበርካታ ዓመታት የግብርና ናሙና ጥናቶች ሲያካሂድ የቆየ በመሆኑ በብሔራዊ ደረጃ የግብርና ቆጠራ ለማካሄድ የሚያስችሉ ልምዶችን አካብቷል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ በቋሚ ሰብሎች፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በሥራ ሥር፣ በከብት አርቢ አካባቢና በከተሞች ግብርና ነክ ጥናቶች ቀደም ሲል ባለመካሄዱና እንደዚሁም ለግብርና ቆጠራ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገው በጀትና የሰው ኃይል በርካታ በመሆኑ ከወዲሁ አስፈላጊው እርምትና ማስተካከያ ለማድረግ እንዲቻል የሙከራ ቆጠራ ጥናት በአብዛኛው የተካሄደ ቢሆንም በተለይ በከብት አርቢ አካባቢ፣ በትላልቅ እርሻዎችና በከተሞች ላይ የሙከራ ጥናቱ በዚህ በጀት ዓመት የሚካሄድ ይሆናል ፡፡

- የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ዓላማዎች

የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- ለብሔራዊ የግብርና ቆጠራ መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መጠይቆች በቆጠራው የሚያስፈልጉትን መረጃዎች በትክክል ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መሆናቸውን ለመገምገምና ለማረጋገጥ፣
- ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ተቆጣጣሪዎች የሥልጠና መመሪያዎችና የሥልጠናው አጠቃላይ ሁኔታ ለመገምገም እንደዚሁም በየደረጃው ለሚካሄድ የሥልጠና ፕሮግራሞች የሚያስፈልገውን የጊዜ መጠን ለመገመት፣
- የመረጃ አቀነባበርና ሪፖርት ዝግጅት ሥራን ለመገምገምና የሚፈለጉ የቆጠራ ውጤቶች በትክክል ለማውጣት የሚቻል መሆኑን ለማረጋገጥ፣
- በአጠቃላይ የብሔራዊ ግብርና የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታዎችን፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለማወቅና ለመገምገም ብሎም መፍትሔዎቻቸውን ከወዲሁ ለመፈለግና አዳዲስ የአሠራር ስልቶችን ለመቀየስ፣
- በተለይም በብዛት የቤት እንስሳት ይገኙበታል ተብሎ የሚገመተው የከብት አርቢዎች አካባቢ ሁኔታ ለማወቅ፣ እንደዚሁም በትላልቅና በንግድ እርሻዎች ላይ የሚካሄደው የግብርና ቆጠራ በምን ዓይነት ማጥናት እንደሚቻል ለመገምገም ናቸው፡፡

- <u>በግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

የግብርና መረጃዎች በትላልቅ የመንግሥትና የግል የንግድ እርሻዎች፣ በከተማዎችና በከብት እርቢ አካባቢዎች የሚሰበሰቡ ሲሆን በሙከራ ቆጠራው የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

